# የአማራ ህዝብ አይንህን ግለጥ! ሴረኞችን አጋልጥ!

ኢሳት ግንቦት 7 (ሥሙን በመጥራቴ ይቀፈኛል!) HR-128ን የተመለከተ 3 ክፍል ያለው ዝግጅት አቅርቦ ነበር።
በሚገርም ሁኔታ HR-128ን ለኮንግረስ የሚያቀርበው ቡድን መሪ (Chairman) ወጣት ቴዎድሮስ ትርፌን ግን አንድም ቦታ ላይ አላስገባውም።




**HR-128ን ለኮንግረስ የሚያቀርበው ቡድን መሪ (Chairman) ወጣት ቴዎድሮስ ትርፌ**

እጅግ የሚገርመው ደግሞ ባለፈው ጃንዋሪ ላይ ዋሽንግተን ዲሲ ካፒቴል ሂል ከኮንግረስ ጋር ስለ HR-128 ምክክር ከተደረገ በኋላ ሌሎቹን ቃለ-መጠይቅ ሲያደርጉ እርሱን አግለውታል፣ አልጠየቁትም። ይህንን በቦታው ተገኝቼ ያረጋገጥኩት ሃቅ ነው። አሁንም ደገሙት!

በአጭሩ ቴዎድሮስ ትርፌ የተገለለው አማራን አትንኩ፤ የአማራን ሰብአዊ መብት የምትጥስ ኢትዮጵያ ልታስብበት ይገባል በማለቱ ነው።

የቡድን መሪው (Chairman) እያለ የቡድኑ አባላት በጉዳዩ ላይ መግለጫ ሲሰጡ እንደማየት እንቆቅልሽ የለም።
እናድርግ እንኳን ቢባል HR-128ን ለኮንግረስ ያቀረቡት ድርጅቶች (አምስት ናቸው እንርሱም አንደኛው የአማራዎች ማህበር በሰሜን አሜሪካ (AAA)፣ ሁለቱ በኢትዮጵያ ስም የሚንቀሳቀሱ፣ አንድ የኦሮሞ ድርጅት እና አንድ TASSC የሚባል ግብረ ሰናይ ድርጅት ናቸው) ተወካዮች መቅረብ

ይገባቸዋል። ይህ ካልተሳካ ግን መሪው ቴዎድሮስ ትርፌ መቅረብ ነበረበት። ነገር ግን ቴዎድሮስ ትርፌ እድል ካገኘ አማራ ማለቱ ስለማይቀር ድምፁ ታፈነ! አሳፋሪዎች! እሳት ግንቦት7 ቀለላቹህ አፈርንባችሁ

ለማንኛውም ወጣት ቴዎድሮስ ትርፌን እኛ አማሮች በሰራው አኩሪ ተግባር እናደንቀዋለን፣ እንደግፈዋለን፣ እናበረታታዋለን!

**HR_128 በወጣት ቴዎድሮስ ትርፌ መሪነት የተገኘ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው።**

**ማስታወሻ፤** ይህ ከኢሳት የመጠበቅ ጉዳይ አይደለም የማጋለጥ ነው።